# ዩሬካ ሂሳብ (Eureka Math) የወላጆች/አሳዳጊዎች የትምህርት መርጃዎች (ሪሶርሶች)

ከታች ያለው ሠንጠረዥ በዩሬካ ሂሳብ (Eureka Math) ቤተሰቦችን ለመደገፍ ያሉትን ብዙ ምንጮች ይዘረዝራል/ይገልጻል። በክፍል ውስጥ ትምህርትን ለመደገፍ ያሉትን አብዛኛዎቹን መገልገያዎች የልጅዎ መምህር ዓመቱን ሙሉ ያጋራዎታል።

| ሪሶርስ | መግለጫ |
|---|---|
| የእንኳን ደህና መጣችሁ ደብዳቤ | ይህ ደብዳቤ ስለ ዩሬካ ሂሳብ ፕሮግራም (Eureka Math program) አጠቃላይ መግለጫ ይሰጣል። |
| የካርድ መጫወቻዎች | ዩሬካ ሒሳብ ተማሪዎች የሂሳብ ልምድ እንዲኖራቸው፣ በፅንሰ-ሀሳብ እና በአተገባበር እንዲረዱት ያስተምራቸዋል። ተማሪዎችን በገሃዱ ዓለም ሂሳብን በሚጠቀሙበት መንገድ ማስተማር የተሻለ እንደሆነ ይሰማናል። የእኛ ዩሬካ የሂሳብ ካርድ ጨዋታዎች የሂሳብ ቅልጥፍናን በአስደሳች እና አሳታፊ መንገድ ለመገንባት የተዘጋጁ ናቸው። የዩሬካ ሂሳብ ካርዶችን ወይም ጨዋታዎቹን በማንኛውም መደበኛ ወለል ላይ መጫወት ይችላሉ። |
| የወላጅ ጠቃሚ ፍንጭ የሚሰጡ ገጾች/የወላጅ ጋዜጣ | Eureka Math የተጠቀሙ ስልቶችን እና ሞዴሎችን፣ ቁልፍ ቃላትን እና በቤት ውስጥ መማርን እንዴት መደገፍ እንደሚችሉ ጠቃሚ ምክሮችን ያካተቱ ተከታታይ የወላጅ ጠቃሚ ምክሮችን በየርዕሱ ያቀርባል። ጀማሪ መዋእለ ህጻናት እና ቅድመ መዋዕለ ህጻናት (K. Pre-K) ተማሪዎች ይህንን መረጃ ከወላጅ ጋዜጣ በእንግሊዘኛ እና በስፓኒሽ ያገኛሉ። |
| ፍኖተ ካርታ | ፍኖተ ካርታ ልጅዎ በሚመጣው አመት ምን እንደሚያጠና/እንደምታጠና የሚገልጽ ሲሆን ከክፍል ውጭ ትምህርትን ለማመቻቸት ሊተገበሩ የሚችሏቸውን ስልቶች ያስረዳል። እነዚህ ክፍል-ተኮር ፍኖተ ካርታዎች በአንድ ወቅት በሒሳብ ትምህርት ይሰጥበት በነበረበት መንገድ እና በዩሬካ ሒሳብ ጥቅም ላይ በሚውሉ ቴክኒኮች መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳለጥ ጥሩ መንገድ ናቸው። K ክፍል ጀምሮ በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽኛ ይሰጣል። |
| የቤት ሥራ ረዳቶች | እያንዳንዱ የቤት ስራ ለዩሬካ ሂሳብ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን እንዲለማመዱ እና ከስሌቱ ጀርባ ያለውን "ለምን" የበለጠ እንዲረዱ እድል ይሰጣል። አሁን ወላጆች በዩሬካ ሒሳብ አስተማሪ-የተጻፉትን የቤት ሥራ አጋዦችን በመጠቀም ልጆቻቸውን በቤት ሥራ ጊዜ በቀላሉ መርዳት ይችላሉ። የቤት ስራ ረዳቶች እንዴት (እና ለምን!) ደረጃ በደረጃ ማብራሪያ ይሰጣሉ። በዩሬካ ሒሳብ የቤት ሥራ ውስጥ ከሚገኙት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት። የቤት ስራ ረዳቶች፥ ወላጆች ልጆቻቸው የቤት ስራ ፕሮብሌሞችን ሲያጠናቅቁ አስተሳሰባቸውን ሲያብራሩ የሚሰሟቸውን የቋንቋ ምሳሌዎችን ይሰጣሉ። |
| አሠራሩን የሚገመገምበት ስልት | ዩሬካ ሒሳብ በመሃከለኛ እና በሞጁል የመጨረሻ ምዘናዎች አጣርቶ ወደ ማወቅ የሚደረገውን ሂደት የሚያብራራ እና ስኬትን ከ 1-4 ሚዛን የሚገመግሙ ቃላቶችን ይሰጣል። በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ያለው እርምጃ በደረጃው ከተማሪ ሥራ የሚጠበቁትን ባህሪያት ይገልጻል። |